# ሐዋርያት በዚህ ዘመን አሉን?

አማኑኤል እንዳለ

“…ነገር ግን ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለ ተሰጠው እምነት ለመምከር እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ”
ይሁዳ3

# ሐዋርያነት

የቃሉ ትርጉም

<<የተላከ መልዕክተኛ ማለት ነው>> በላኪው ስለሚመረጥ ተላኪው የላኪውን ትዕዛዝ እና ሐሳብ የሚያስፈጽም ባለሟል ነው። (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት)

ሐዋርያ የሚለው የአማርኛ ቃል በግሪክ አፖስትሎስ የሚለውን ቃል የሚተካ ሲሆን ቃሉ፣ ከላይ የያዝነውን አይነት ትርጉም ይይዛል።

በጥንታዊ ግሪክ ኣፖስትሎስ የሚለው ቃል የሚወክለው ትርጉምን ስንመለከት

"In older Greek the term is a nautical one denoting a freighter or a naval force with no sense of initiative or authorization. Hence it doesn't become a term for envoy as in the NT, nor do the LXX, Josephus, or Philo form a link at this point to the distinctive and unusual NT usage" Theological Dictionary of New Testament (Kittel's 1st volume)

በጥንታዊ ግሪኮች ዘንድ ሆነ በእነ ጆሲፈስ ወይም ፊሎ አጠቃቀም አፖስትሎስ የሚለው ቃል አጠቃቀማቸው በአዲስ ኪዳን ቃሉ ከዋለበት እና ከሰጠው ትርጉም ትንሽ ለየት ያለ ነው። ትርጉሙም አንድ ስለ የባህር ሐይል ወታደር ሆኖ ነገር ግን ስለ ባህር ሐይል የመረዳት ችሎታ የሌለው ነው።

አፖስትሎስ የሚለው ቃል ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ የያዘው ትርጉም ደግሞ

"በመቄዶኒያ ላሉት ችግረኞች መስጠትን በተመለከተ <ሐዋርያ> በ 2ቆሮ 8፡23 ላይ ስለ "ቲቶ" እና ሌሎች ወንድሞችን በተመለከተ በቆሮንቶስ ላልች ቤተ ክርስቲያን በገለጻው ውስጥ "መልዕክተኞች" በማለት ይቀበሏቸው ዘንድ አሳስቧቸዋል። እንዲሁም ለፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን አፍሪዲጥንን በተመለከተ ሲናገር (ፊል 2፡25) አፖስትሎስ የሆነውን በማለት የቃሉን ትርጉም መልዕክተኛ በማለት ግልጽ ያደርግልናል።" Vine's Expository Dictionary of New testament Words

ስለዚህ ለቃሉ የምንሰጠው ትርጉም በዋናነት "መልዕክተኛ" የሚለውን ይሆናል ማለት ነው።

## 12'ቱ ሐዋርያት

አስራ ሁለቱ የጌታ ሐዋርያት በመጽሐፍ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ሐዋርያ በምናጠና ጊዜ የምናገኘው ነው። ማርቆስ 3፡14 << ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ለስብከትም ይልካቸው ዘንድ ዐሥራ ሁለቱን ሾማቸው ሐዋርያትም ብሎ ጠራቸው>> ስለዚህ እነዚህ አስራ ሁለት ሐዋርያት የጌታ ሐዋርያ ሲሆኑ ለአንድ ተልዕኮ መላክን ብቻ ሳይሆን "ሾማቸው" ስለሚል ስልጣንንም የሚያመለክት ነው።

እነዚህ ሐዋርያት በጌታ በቀጥታ የተመረጡ እና የተሾሙ መሆናቸው ግልጽ ስለሆነ ሉቃስ እነደጻፈው በሚታመነው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እነዚህን ሐዋርያት ብቻ ለማመልከት እና በቀጥታ በጌታ የተሾሙ መሆናቸውን ለማሳየት "The twelve", "the twelve apostles" በማለት ይጠቀማል በሐዋርያት ሥራ ላይ ሉቃስሐዋርያ የሚለውን ቃል ሲጠቀም በዚህ መንገድ ሲጠቀም ከላይ ያለውን በጌታ መሾም ለማመልከት ነው ማለት ነው።

## ጳውሎስ እና ማቲያስ

የአስቆሮቱ ይሁዳ ይህንን አገልግሎት በመተው በመሄዱ ፈንታ አስራ አንዱ ሐዋርያት በጋራ በመሆን ልክ እንደ ጌታ በምድር በነበረበት ወቅት አስራ ሁለቱን እንደ ሾማቸው ሁሉ ማቲያስንም ዕጣ ጥለው በአስቆሮቱ ይሁዳ ፈንታ ከአስራ አንዱ ጋር ተቆጠረ።

የማቲያስ ምርጫ ሐዋርያዊ ስልጣን ያለው መሆኑን ለማወቅ በዛው ቦታ ሐዋ 1:25-26 ሐዋርያነትን ብቻ ሳይሆን ሹመትንም በማንሳት ጭምር ለአስራ አንዱ ጋር እንደ ተቆጠረ ይናገራል።

ምን አልባት አንድ ሰው አስቀድመው የተመረጡት ሐዋርያት በቀጥታ በጌታ የተመረጡ ናቸው ይል ይሆናል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር <<ዕጣ በጉያ ውስጥ ይጣላል ውሳኔው በሙሉ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።>> ምሳሌ 16:31 ያረጋግጣል። በሐዋርያት ጸሎት ውስጥም <<አንተ የሰውን ልብ ታውቃለህ ከእነዚህ ከሁለቱ መካከል የመረጥኸውን ሰው አመልክተን>> በማለታቸው ዕጣ ስለጣሉ የማቲያስ መመረጥ አንድም የዚህ ጸሎት መልስ ሲሆን እድል የመሰሉ አጋጣሚዎች እንኳን ፍጻሜያቸው በእግዚአብሔር የሚወሰኑ ስለሆኑ የማቲያስ መመረጥ ልክ እንደቀደሙት አይነት ነው።

ሌላኛው ሐዋርያ ደግሞ ጳውሎስ ነው። ጳውሎስ ጌታ በምድር በሚመላለስበት ጊዜ በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ በቤተ ክርስቲያን ላይ በተፋፋመው ታላቅ ስደት ምክንያት በኣስጢፋኖስ መገደል እጁ እንዳለበት በመናገር ጳውሎስን <<ሳውል>> በማለት ያስተዋውቀናል።

አማኞች ስለ ወንጌል ብለው በሚሰደዱበት ወቅት ሳውል የተባለው ጳውሎስ ወንዶችን ሆነ ሴቶችን አስሮ ወደ ኢየሩሳሌም ለመውሰድ እንዲችል በደማስቆ ለነበሩት ምኩራቦች ድብዳቤ ከካህናቱ እጅ ተቀብሎ ሲጓዝ ጌታ ኢየሱስ በደማስቆ መንገድ ተገናኝቶት ለራሱ መልዕክተኛ አድርጎ ሾመው

<<"ሂድ ይህ ሰው በአሕዛብና በነገሥታት ፊት እምዲሁም በእስራኤል ሕዝብ ፊት ስሜን እንዲሸከም የተመረጠ ዕቃዬ ነው እኔም ስለ ስሜ ምን ያህል መከራ መቀበል እንዳለበት አሳየኣለሁ።" ሐዋ 9:16

ስለዚህ ልክ እንደ አስራሁለቱ ሐዋርያት ሁሉ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጌታ በቀጥታ መመረጡን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

## ሐዋርያነት እንደ ጸጋ ስጦታ

በአዲስ ኪዳን ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በኩል ካፈሰሰው ስጦታዎች ውስጥ ሐዋርያትን በተመለከተ ይናገራል። በዚህም መሠረተ እግዚአብሔር ሐዋርያትን ለቤተ ክርስቲያን መድቦአል (1ኛ ቆሮ 12:28-29)

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሳት ለቤተ ክርስቲያን ካፈሳሰው ስጦታ ውስጥም አንዱ "ሐዋርያነትን" ነው ኤፌ 4:11

በዚህም ምክንያት ከላይ ካየናቸው ውጪም መጽሐፍ ቅዱስ በርናባስን፣አፍሮዲጥን፣ቲቶ፣ይሁዳ እና ሲላስ ሐዋርያት ተብለው ተጠርተዋል።

## አማኞች እንደ ሐዋርያት

ከላይ <ሐዋርያ> የሚለውን ቃል ትርጉም ሰጥተን ስንነሳ የተላከ በሚለው ነበር። ታዲያ አማኞች በሞላ የተላኩ ናቸው። <<እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትደበቅ አትችልም ሰዎችም መብራት አብርተው

ከዕንቅብ ሥር አያስቀምጡትም በቤት ውስጥ ላሉት ሁሉ እንዲያበራ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጡታል እንጂ። እንደዚሁም ሰዎች መላካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ።>> ማቴ 5፡14-16

ከላይ ባለው ምንባብ ውስጥ አማኞች በሞላ ባለንበት ስፍራ ሆነን ይህንን ብርሃን እንድናበራ ተልዕኮ ተሰቶናል። ወንጌልን መናገር በወንጌሉ ድነው የወንጌሉን ተስፋ ከተካ

ፈሎ ሕያው ምስክሮች በሙሉ የሚጠበቅ ነውና በዚህ አግባብ <ሁሉም ክርስቲያን የተላከ > ነው ማለት ይቻላል።

ነገር ግን ይህንን ስንል በ 1ኛ ቆሮ 12፡29 <ሁሉ ሐዋርያት ናቸው?> ሲል መልሱ አይደሉም ነው ይህ ግን ሁሉም ሰው የዚህን የጸጋ ስጦታ ሰላልተቀበለ እንጂ ከላይ ካልነው ጋር የሚቃረን አይነት አድርገን ልናስብ አይገባም።

## የሐዋርያት አገልግሎት እና ሥልጣን

የአስራ ሁለቱን ሐዋርያት እና የጳውሎስን የአግልግሎት እንዲሁም ስልጣን ስንመለከት ሐዋርያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች እና የትምህርት ሀላፊዎች ነበሩ ሐዋ 2፡42 1ኛ ቆሮ 5፡1-5 ሐዋርያቶች ልክ እንደ ነቢያቶች የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን መሠረት ጣዮች ነበሩ ኤፌ 2፡20 1ኛ ቆሮ 3፡10 ለትምህርት እና ለሥነ ምግባር የሚያስፈልግ ሁሉ በእነርሱ በኩል ለቤተ ክርስቲያን ተሰጥቷል ገላ 1፡6-8 ይሁዳ 3

ይህም መመሪያ የሚገኘው በአዲስ ኪዳን ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ጠብቃ አኑራዋለች።

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የነበሩ ወንድሞች የጳውሎስን ሐዋርያነት ጥያኤ በማንሳት እርሱን ሀዋርያ አይደለም ለማለት በመሞከራቸው ምክንያት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለራሱ ሐዋርያነት መከላከያ አቅርቦ ነበር።

ከመከላከያዎች መካከል 1. በቀጥታ በኢየሱስ ክርስቶስ ና በእግዚአብሔር የመመረጡን ሁኔታ ያነሳል( ገላ 1፡1) 2. በቀጥታ መገለጥ መቀበሉ (1ኛ ቆሮ 2፡10, 11፡23, 15፡3)

ከዚህም የተነሳ ይህንን የጳውሎስ "መገለጥ" አለመቀበል በቀጥታ ወደ ሲዖል መግቢያ በር ኣንደሆን በርግጠኝነት ተናገረ <<ቀደም ብለን እንዳልነው አሁንም ደግሜ እላለሁ ማንም ከተቀበላችሁት ሌላ የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ እርሱ ለዘላለም የተረገመ ይሁን።>> ገላ 1፡9

የተሰሎንቄ አማኞችም በሐዋርያት በኩል የተላከላቸውን መልዕክት "እንደ እግዚአብሔር ቃል" ተቀብለዋል።<< ከእኛ የሰማችሁትን የእግዚአብሔርን ቃል በተቀበላችሁት ጊዜ በእናንተ በምታምኑት ዘንድ በርግጥ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ሰላልተቀበላችሁት እግዚአብሔርን ያለ ማቋረጥ እናመሰግናለን።>> 1ኛ ተሰ 2፡13

ስለዚህ በስልጣን ከጌታ ተልከዋልና ቃላቸው እንደ ጌታቸው ቃል የሆኑ የሚሠራ እንደሆን አድርገን ልናስብ ይገባል ማለት ነው።

በኤፌ 2፡20 <<በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል>> የሐዋርያት አገልግሎት የተመዘገበልን በወንጌላት እና በመልዕክታት በኩል እንደምሆኑ ኣንደዚህ ብለን ልናስብ እንችላለን።

በወንጌላት በጌታችን ተሰበከ በሐዋርያት ትምህርት በኩል ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች በመልዕክቶች በኩል ትምህርቶቹ ተብራሩ። ስለዚህ የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት እና ነቢያት የዲስ ኪዳና ቤተ ክርስቲያን መሠረቶች ናቸው።

ለመሆኑ ይህ መሠረት ምንድነው? ስለዚህ መሠረት ሲናገር በኤፌ 3፡5 በድጋሚ ሐዋርያት እና ነቢያት በተመለከተ ይናገራል።

<<ይህም ሚስጢር አሁን ለቅዱሳኑና ሐዋርያትና ነቢያት የተገለጠውን ያህል ባለፉት ዘመናት ለነበሩ ሰዎች አልተገለጠም ነበር። ይህም ምስጢር አሕዛብ በወንጌል አማካይነት ከእስራኤል ጋር አብረው ወራሾች አብረው የአንዱ አካል ብልቶች እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ በመሆን አብረው ተካፋይ መሆናቸው ነው።>>

ስለዚህ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት በኩል መሠረት የሚጣልበትን ትምህርት እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የገለጠው በእነርሱ በኩል ነው።

ይህ አግልግሎት ከላይ ባየናቸው በሁለቱ በኩል ተፈጽሟል ለምሳሌ በርናባስ በአንጾኪያ የነበረውን የወንጌል ሁኔታ በኢየሩሳሌም ያሉ ሐዋርያት ካዳመጡ በኋላ በርናባስን ወደዚያ በመላክ ይጎበኛቸው ዘንድ ልከውት ነበር። በዚያ ጊዜ በርናባስ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን ወደ አንጾኪያ ፈልጎ በመምጣት አንድ አመት በሙሉ አስተማሩ ወይም መሰረትን ጣሉ። ስለዚህ እነዚህ መሠረት ጣዮች ሐዋርያቶች ብቻ ናቸው።

## ታዲያ በዚህ ዘመን ሐዋርያት አሉን?

ከላይ በሰፊው ባቀረብነው ሐቲት ውስጥ ሐዋርያት አሉ የምንል ከሆነ አሁንም መሠረት ይጥላሉ ማለታችን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመሠረቱ ላይ መታነጻችንን እየተናገረን ሳለ አሁንም ሌላ መሠረት እንዳል አድርገን ልናስብ አይገባም። በተጨማሪም ሐይማኖተ አበው ስለ ቅዱሳት መጽሐፍት ከሰጡት ምሥክርነት በመቃረን እንገኛለን <<የማይሻር የማይሳሳት ፍጹም ስልጣን ያለው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፉ 66 መጻሕፍት የያዘ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናምናለን። እንዲሁም በሰው እምነት እና ሕይወት ላይ የመጨረሻ ስልጣን ያለው የቤተ ክርስቲያን እምነት እና ሥርዐት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ መሆኑን እናምናለን።>> ሐይማኖተ አበው ቀኖና መጽሐፍ ቅዱስ

በሐገራችን ኢትዮጵያ ካሉ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ካሪዝማዊ እና ጴንጤቆስጤያዊ "ቤተ ክርስቲያን" ሐዋርያት አሉ በማለት አንዳንድ ሰዎችን "ሐዋርያ" በማለት ሲሾሙ ይታያል ይህ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ውጪ መሆን ነው።

ስለ ሐዋርያዊ ሥልጣን ስንናገር ቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ እንዳለው ዓይነት ሥልጣን አለው ማለታችን ነው ይህ ማለት ልክ ንግግራቸው ሆነ ትዕዛዛቸው እንደ እግዚአብሔር ቃል ይወሰዳል ማለት ነው።

<< ማንም ነቢይ ነኝ የሚል መንፈሳዊ ስጦታ አለኝ የሚል ቢኖር ይህ የጻፍሁላችሁ የጌታ ቶዛዝ መሆኑን ይወቅ ይህን የማያውቅ ቢሆን ግን ኣርሱም አይታወቅ።>> 1ኛ ቆሮ 14፡38

<<የሰበኩላችሁን ቃል አጥብቃችሁ ብትይዙ በዚህ ወንጌል ትድናላችሁ አለዚያ ያመናችሁት በከንቱ ነው።>> 1ኛ ቆሮ 15፡2

የቤተ ክርስቲያን መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ የእምነት እና የልምምድ ደንቦች በቅዱስ መጽሐፍት ተሰቶናል እነርሱ ብቁ እና በቂ ስለሆኑ አሁን በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት ነን ባዮችን ልትቀበል ሳይሆን እንደ ቅዱስ መጽሐፍ አግባብ ልታወግዝ ይገባል ምክንያቱም መሠረቱ ተጥሏል ይላልና (ኤፌ 2፡20) መሠረታቸው በቅዱስ መጽሐፍ የተዘረዘሩት የእምነት እና የልምምድ ደንቦች ተቀምጠውልናል ስለዚህ ሐዋርያ አለ ስንል ከዚህ ታላቅ የተሀድሶ እምነት ከነበረው አንዱ ጋር እይተላተምን ነው (መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ)።።

ስለዚህ ቅዱሳን ሐዋርያት በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል ቤተ ክርስቲያን ከምስረታ ጀምሮ እስከ ፍጹምነት ደረጃ ድረስ ኣስክትደርስ በቃሉ በኩል ያንጿታል ማለት ነው እንጂ አሁን ባለንበት ዘመን ድረስ ሐዋርያትን እየሰጠ አያንጻትም ይልቅ ሕያው በሆነው በቅዱስ ቃሉ በኩል ቤተ ክርስቲያንን ያንጻታል።

<<በቃሉ አማክይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት እንድትቀደስ>> ኤፌ 5፡26

## ሚሶናዊያን (Missionary)

Missionary (noun): a person who is sent to foreign country to do religious work (such as to convince people to join a religion or to help people who are sick, poor, etc.

(Merriam Webster Dictionary)

ይህንን ሐሳብ ያነሳሁበት ምክንያት ብዙ ሰዎች ሐዋርያነትን ከላይ ትኩረት በሰጠሁበት ሐሳብ ሳይሆን ከወንጌል ሰባኪነት ጋር አያይዘው በመመልከት ይኸው እከሌ "ሐዋርያ" ነው በማለት ስለሚናገሩ ነው።

በእርግጥ ሐዋርያት ወንጌል ባልገባበት ቦታ ወንጌልን ያደርሱ ነበር <<ለሌሎች ሐዋርያ ባልሆን እንኳ ለእናንተ ግን በርግጥ ሐዋርያ ነኝ ምክንያቱም በጌታ የሐዋርያነቴ ማኅተም እናንተ ናችሁ።>> 1ኛ ቆሮ 9፡2

<<ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።>> ማቴ 28፡18-20

ስለዚህ ከሐዋርያት አገልግሎት ጋር በተያያዘ የምሥራቹን መናገር ለዚህ ታላቁ ተልዕኮ እስከ ፍጻሜ ድረስ በመጓዝ ሰማዕት እስከመሆን በመድረስ በዚህ ዘመን ለአማኞች ሁሉ የእምነት አባቶች በመባል ይታወቁ ዘንድ በጽናት ኖረዋል።

ይህ ታላቅ ተልዕኮ ሁሉንም አማኝዕች የሚመለከት እና ሁሉም አማኝ የምሥራቹን ሊናገር መዳን በጌታ በኢየሱስ ብቻ መሆኑን ሊያውጅ ተልኳል።

ነገር ግን ምንም ሁሉም ሰው በያለበት የምሥራቹን ቢሰብክም ልክ እንደ ሐዋርያት ወንጌል ወዳልደረሰበት የምስራቹን ወዳልደረሰበት በመሄድ የሚሰብኩም የሚከታተሉ ነበሩ <<ሐዋርያትና በይሁዳ የነበሩት ወንድሞች አሕዛብ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ተቀበሉ ሰሙ ስለዚህ ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም በወጣ ጊዜ ከተገረዙት ወገን የነበሩ አማኞች ነቀፉት>> ሐዋ 11፡1-2

ስለዚህ ከወንጌለ ስብከት ጋር በተለየ ይህንን አገልግሎት በሙሉ ጊዜ እና ጉልበት ለማገልገል ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የሚመጡ ቤተ ሰቦቻቸውን የሚተዉ ከሞቀ ኑሮአቸው ትተው ወደ በረሃ የሚጓዙ ጌታ ጸጋ ያበዛላቸውን ወንድም እና እህቶችን በተመለከተ ሚሲዮናዊ ወይም ሚሽነሪ ብለን ልንጠራ እንጂ <ሐዋርያ> ልንል አይገባም ይህ በሁለት ምክንያት ነው

1ኛ በቅዱሳት ላሉ ሐዋርያት ላልን ክብር

2ኛ ሐዋርያቱ ወንጌል ሰባኪዎች ብቻ ሳይሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሠረቶች ሰለሆኑ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላሉት ሐዋርያት ክብር ስንል እነርሱ በቀጥታ በጌታ የተመረጡ እና ከምንጩ የጠቀበሉ ናቸው ምንም በዚህ ዘመን ሰዎች ለወንጌል ልባቸው ቢከብድም እንደ እነርሱ በቀጥታ ሳይሆን ሐዋርያቱ ከጌታ የተቀበሉትን ከቅዱሳት መጽሐፍት በማግኘት ነውና ልዩነቱ ግልጽ ነው። እነርሱ ቃላቸው እንደ ሚሰራ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆኑ እና ሰዎችም ቃላቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል መቀበላቸው እነርሱን ልናከብር ይገባል።

የቤተ ክርስቲያን መሠረቶች ናቸው የሚለውን መሠረት ጣዮች ናቸው በሚለው ነው። አንድ ቤት ከሁሉም ነገር አስቀድሞ መሠረት መጣል አለበት መሠረት ከተጣለ ወዲያ ሁሉም መሠረቱ ላይ የሚቀጥል ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ልክ እንደ ቤት በመሳል ሐዋርያት እና ነቢያትን ደግሞ መሠረት ጣዮች ናቸው በማለት ይገልጻቸዋኣል። ታዲያ ሐዋርያት እና ነቢያት የቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆኑ ትምህርቶችን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በመቀበል የማትታየው ነገር ሁሉን አቀፍ ለሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሠረት ጣሉ። ይህንንም ሲገልጽ በሐዋርያት እና በነቢያት መሠረት ላይ በማለት ነው።

ስለዚህ የአንድ ቤት መሠረት ተገንብቶ አልቆ አሁን ቅዱሳን በዚህ መሰረት ላይ የማእዘን ድንጋይ ወደ ሆነው ሕያው አለት ክርስቶስ እናድጋለን። አሁን ሐዋርያት አሉ የምንል ከሆነ ከዚህ ምንባብ ጋር መላተማችን ይሆናል ማለት ነው።

እነዚህን የቅዱሳን ሐዋርያት እና የወንጌል ሰባኪዎችን ልዩነት በደንብ ለማጉላት ለእነዚህ አይነት ሰዎች መስተት የሚገባን ሙያዊ ስም ሚሲዮናዊያን የሚለው ይሆናል፣

ሚሲዮናዊያን ከሐዋርያት የተቀበሉትን እውነተኛ ትምህርት ሳይቀንሱ ሳይጨምሩ ሊያስተምሩ ይገባል እንጂ ሐዋርያት ሊባሉ አይገባቸው።